የዚህ ተዕይንት አካል ሁነን፣ ዝማሬያቸውን እየዘመርን ትርጉም እንድምታ ያለው ሕይወት ወደሚወረስበት የገድል የድል ጉዳና ማምራት የዚያ የጀግና ትውልድ የአጥንቱ ፍላጭ፣ የሥጋው ክፋይ የሆንን ሁሉ ዕድል ፈንታችን ዕጣ ተርታችን ነው ይላል ኢሕአፓ::

ፋሽስቶች የሚሰፈሩበትን የየካቲት ቁና ቀድመውን ያለፉት ታጋዮች ብዙ ዙር አዙረውልናል:: ቀሪው ዙር እኛን ቀሪዎችን ይጠባበቃል:: የቁናው ዙር እንዲሞላና ቁናቸውን እንዲያገኙ ዕምነታችን ሰበዝ አክርማ፣ አንድነታችን አለላ ሁኖ መቅረብ ይጠበቅበታል::

አሁንም አሁንም አንድ የካቲት አልፎ ሌላ የካቲት ሲተካ—ኢሕአፓ በትግሉ ላይ ያለው አቋም የማይተካና የማይለወጥ ነው::—

የካቲት በሕዝባዊ አመጽ ይወለዳል !

እ ና ቸ ን ፋ ለ ን ! ! !

የ ጎሠሪያ